# *Alexandria City Public Schools*

## የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት (Family Life Education)፤ 6ተኛ ክፍል ውስጥ

***ዳግም-ምልከታ ለማድረግ ያለ-መብት:*** ወላጆች እና አሳዳጊዎች፤ በትምህርት ቤት ክፍሉ/division የሚሰጠውን፤ በፕሮግራሙ ውስጥ ጥቅም-ላይ የሚውለውን የጽሁፍ እና የድምፅ-እይታ (audio-visual) ትምህርትን ቁሳቁሶችን ጨምሮ፤ የ'Family Life Education Program'ን በድጋሚ-የመመልከት መብት አላቸው። ወላጆች እና አሳዳጊዎች፤ ልጃቸውን ከ'Family Life Education' የትምህርት-አሰጣጥ፣ ከሁሉም ወይም ከተወሰነው-ከዚህ ክፍል እንዲወጡ-ፈቃድ እንዲያገኙ የማድረግ መብት-አላቸው።

***የፕሮግራም ግቦች:*** የACPS፣ የ'Family Life Education' ስርዓተ-ትምህርት፤ ሁሉን-አቀፍ የሆነ፣ ቅደም-ተከተል ያለው ከK-12 ፕሮግራም ሆኖ፤ በቤተሰብ አኗኗር እና በማህበረሰ ግንኙነቶች ላይ - ለዕድሜያቸው-ተገቢ በሆነ የትምህርት-አሰጣጥን አካትቶ እንዲቀርብ የተቀረጸ ነው። የትምህርት-አሰጣጡ የተቀረጸው፤ ሊኖር-የሚያስፈልገውን የወላጅ ተሳትፎን ለማበረታታት፣ አዎንታዊ የሆነ የራስ-ጽንሰ-ሃሳቦችን ለማሳደግ እና ከእኩዮቻቸው-ጋር እኩል-ሆኖ ለመታየት ሲባል - የሚመጣባቸው ጫና መቋቋሚያ፣  እና እንደ ተማሪዎቹ የዕድገት ደረጃዎች እና አቅሞች መሠረት - በዘመናዊ አኗኗር ውስጥ የሚገጥማቸውን ጫናዎች የሚቋቋሙበትን መንገዶች ማቅረብ ነው።

***የፕሮግራም ቅደም-ተከተል:*** በቨርጅኒያ የትምህርት መምሪያ (Virginia Department of Education) በታዘዘው-መሠረት፣ በACPS ውስጥ፣ የ'Family Life Education' ስርዓተ-ትምህርት፣ ከK-10ኛ ክፍሎች - በሚከተሉትን የጽንሰ-ሃሳብ ይዘቶች ላይ በ[Standards of Learning]ላይ መሠረት አድርጎ የትምህርት-አሰጣትን ያካትታል:

1. የቤተሰብ አኗኗር እና የማህበረሰብ ግንኙነቶች፤
2. የቤተሰብ ግንኙነቶች ያላቸው ከፍተኛ-ዋጋ፤
3. የወሲባዊ-እንቅስቃሴዎችን - ወደ ሌላ ጊዜ ማስተላለፍ ያለው ከፍተኛ ዋጋ፤
4. የመታቀብ ትምህርት፤
5. ለወንዶች፣ ሴቶች፣ ልጆች፣ እና ማህበረሰቦች፤ ጋብቻ ያለውን - ጥቅሞች፣ አስቸጋሪ-ፈታኝ ነገሮች፣ ኃላፊነቶች እና ያለውን ከፍተኛ ዋጋ፤
6. የሰው-ልጅ ወሲባዊ-መለያ (Human sexuality)፤
7. የሰው-ልጅ መራባት/መዋለድ (Human reproduction)፤
8. ያልታሰበ እርግዝና በሚፈጠር ጊዜ፤ ለማደጎ-የመስጠትን አዎንታዊ የሆነ አማራጭ - ያለው ጥቅሞች፤
9. በወሲብ የሚተላለፉ በሽታዎች፤ መንስዔ፣ መከላከያ፣ እና የሚያመጡት ችግሮች፤
10. የሰውን-ልጅ ከቦታ-ቦታ ያለፈቃድ ዝውውር (human trafficking)ን መከላከል፤
11. የፍቅር-ጓደኝነት ጥሰት (dating violence) - በዚህ ውስጥ መካተት ያለበት፤ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ ማንኛውም የወሲብ ክንውን ከማድረጋቸው በፊት ስምምነት መስጠት፣ ጥቃት-ያለባቸውን የግንኙነት ፀባዮችን ማወቅ፣ የወሲብ ጥቃትን ለመከላከል የሚወሰዱ እርምጃዎችን፣ ሊገኙ-የሚችሉትን የማማከር እና ሕጋዊ የመረጃ-ምንጮችን ማወቅ፣ እና፣ የወሲብ-ጥቃት በሚከሰት ጊዜ - ወዲያውኑ የሕክምና ትኩርት እና ምክርን ማግኘት ጠቃሚነትን፣ እንዲሁም የሕግን አስፈላጊነት፤ እንዲያውቁ ማድረግን ያካትታል፤ እና
12. የአዕምሮ ጤና ትምህርት እና ግንዛቤ።

***የስርዓተ-ትምህርት መስመሮች (Strands):*** ስርዓተ-ትምህርቱ፤ በአራት የመለኪያ ርዕሶች (measurement topics) ዙሪያ የተገነባ - ይህም ጭብጥ-ያለው መስመር (thematic strands)፣ እና የሂደት መደበኛዎች - ግንዛቤዎችን ዘላቂ በማድረግ እና መሠረታዊነት ያላቸውን ሂደቶች በፕሮግራሞ መሃከል-ላይ በማድረግ ላይ ትኩረት አድርጎ-የተገነባ ነው።

1. የግል ጤና እና ጤናማነትን ጠብቆ-መቆየት (Puberty)
2. የሰው-ልጅ መራባት/መባዛት (Human Reproduction)
3. የየግል የደህንነት-ጥበቃ (Personal Safety)
4. ተፅዕኖዎችን መተንተን

ለእያንዳንዱ ክፍል - ከእነዚህ የመለኪያ ርዕሶች (measurement topics) ጋር ጎን-ለጎን በማድረግ፤ ግቦችን ማስተላለፍ እና የክንውን-ሂደቶችን ይገመግማል።

*ስርዓተ-ትምህርትን ለአንዳፍታ-በምልከታ-ላይ:* በ6ኛ ክፍል የ'FLE' የትምህርት አሰጣጡ ወቅት፤ የሚከተሉት ርዕሶች ላይ - ምላሽ-ተሰጥቶባቸዋል።

# የ6ኛ ክፍል - የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት

<table>
<tr><td></td><td><u>ክፍል/Unit 1:</u> የ'Puberty' ለውጦች<br><br>በዚህ ክፍል/unit ውስጥ፤ ተማሪዎች - በ'puberty' ወቅት የተፈጠሩትን፣ አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ እና ስሜታዊ ለውጦቻቸውን ይፈትሻሉ። በዚህ ጊዜ ውስጥ፣ የየግል የንጽህና አጠባበቅ ልምዶችን በተስፋፋ-ሁኔታ ማስፈለጋቸውን - ተማሪዎች ይረዳሉ። በወንድ እና ሴት ላይ ባሉት የለውጦች መለያየት ላይ፣ ይወያያሉ።<br><br>1. ትምህርት/Lesson 1፡ እየተቀየረ-ያለው አካላችን (Our Changing Bodies) – ለአቅመ-አዳም/አቅመ-ሄዋን መድረስ (puberty) ወቅት፤ በአካላዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የጽዳት-በጥበቃ ላይ የሚከሰቱ ለውጦችን መለየት።<br>2. ትምህርት/Lesson 2፡ ከወንድ ከ- ሴት ጋር ያሉ ለውጦች (Male Vs. Female Changes) - ለአቅመ-አዳም/አቅመ-ሄዋን መድረስ (puberty) ወቅት ላይ፤ በወንዶች እና በሴቶች ላይ በሚከሰቱት ለውጦች መካከል ያለውን ልዩነት መለየት።</td><td>መደበኛ-ደረጃ ያለው መማር<br>(Standards of Learning):<br>6.1, 6.2, 6.3</td></tr>
<tr><td></td><td><u>ክፍል/Unit 2:</u> የሰው-ልጅ መራባት/መባዛት (Human Reproduction)<br><br>በዚህ ክፍል/unit ውስጥ፤ ተማሪዎች - በወንድ እና ሴት የመራባት (reproduction) ሂደት ላይ አጠቃለው የሚማሩ ይሆናል። ተማሪዎች፤ በወሲባዊ እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ የሚያመጣውን አደጋዎች ያስረዳሉ። ተማሪዎች፣ ስለ'STDS' እና ስለ'HIV' ስርጭት፣ መሠረታዊ-የሆኑ እውነታዎች ላይ የተማሩትን ያስታውሳሉ።<br><br>1. ትምህርት/Lesson 1፡ የወንድ እና የሴት የመዋለድ-ሁኔታ (Male and Female Reproduction) - የወንድ እና የሴት የመራቢያ ዘዴን - የአካል ክፍሎችን እና ተግባራቸውን መለየት እና መግለጽ።<br>2. ትምህርት/Lesson 2፡ በወሲብ የሚተላለፉ በሽታዎች (Sexual Transmitted Diseases) - በወሲባዊ (sexual) እንቅስቃሴ በመሳተፍ ሊመጡ የሚችሉ አደጋዎችን፣ እና በወሲብ የሚተላለፉ በሽታዎችን ስርጭት እና ያልተፈለገ-እርግዝናዎችን የመከላከያ መንገዶችን መወያየት።<br>3. ትምህርት/Lesson 3፡ HIV & Aids – 'HIV' እንዴት እንደሚተላለፍ - መወያየት።</td><td>መደበኛ-ደረጃ ያለው መማር<br>(Standards of Learning):<br>6.4, 6.5, 6.6, 6.9</td></tr>
<tr><td></td><td><u>ክፍል/Unit 3:</u> የየግል የደህንነት-ጥበቃ (Personal Safety)<br><br>በዚህ ክፍል/unit ውስጥ፤ የተለያዩ ዓይነት፣ ጥቃት፣ የጥቃት ምልከቶች እና ለሚያምኑት አዋቂ-ሰው ጥቃቱ እንደተፈጠረ ሪፖርት የማድረግን ጠቃሚነት፤ ተማሪዎች ግንዛቤ እንዲያገኙ ይደረጋል። የልጅ-ጥቃት (child abuse)ን እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንደሚቻል እና የሚሰጥ-ህክምና ላይ የመረጃ-ምንጮችን (Resources) የሚያገኙበት-መንገድ ይገለፃል።<br><br>1. ትምህርት/Lesson 1፡ የግል የደህንነት ጥበቃ እና ጥቃት (Personal Safety and Abuse) - 6ቱን ዓይነት የጥቃት-ዓይነት መለየት (አካላዊ፣ የቃላት-ትንኮሳ፣ ስሜታዊ፣ ወሲባዊ፣ ቸል-ማለት፣ እና የኤሌክትሮኒክ (Electronic)/ማህበራዊ ሚዲያ (Social Media)፤ እና እነዚህን ጥቃቶች እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንደሚቻል መረዳት።</td><td>መደበኛ-ደረጃ ያለው መማር<br>(Standards of Learning):<br>6.8</td></tr>
</table>

**ክፍል/Unit 4:** ***ተፅዕኖዎችን መተንተን***

ይህ ክፍል - ተማሪዎች፣ እንዴት የመገናኛ-ብዙሃን (mass media) መልዕክቶች - የወሲባዊ እና የፆታ ስቴሪዮታይፐ-አመለካከት (stereotyping) ሃሳቦቻቸው ላይ ተጽዕኖ እንደሚያደርሱ እንዲመረምሩ ያደርጋቸዋል። አደዛዥ-ዕፅ - በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ስለሚያደርሰው ተጽዕኖ - ተማሪዎች ይገነዘባሉ። ተማሪዎች - ችግርን መፍታት እና የግንኙነት-ችሎታዎች ላይ፣ የሚለማመዱ ይሆናል።

1. **ትምህርት/Lesson 1፡ ማህበረሰብ እና የፆታ-መገለጫ (Society and Sexuality) –** Discuss the ከፆታ መገለጫ እና የፆታ ስቴሪዮታይፐ (gender stereotyping) ጋር ግንኙነት ባላቸው በርካታ-የሆኑ ከማህበረሰብ-ጋር ግንኙነት ያላቸውን መልዕክቶች ጋር መወያየት፣ እና በማህበረሰቡ-ውስጥ ስለሚገኙ አዎታዊ (positive) እና አሉታዊ (negative) መልዕክቶች ያለውን ልዩነት መለየት።
2. **ትምህርት/Lesson 2፡ የአደንዛዥ ዕፅ መጠቀም እና አላግባብ-ጥቅም ላይ ማዋል (Substance Use and Abuse) -** አደንዛዥ ዕፅን መጠቀም እና አለአግባብ-ጥቅም ላይ ማዋል በግል እና ውሳኔ-በመወሰን አቅማቸው ላይ ያለውን ተጽዕኖ ሊኖረው መቻሉን መለየት።
3. **ትምህርት/Lesson 3፡ የ'Draw the Line/Respect the Line'ን ማስተዋወቅ –** መስመሩን የማስመር (draw the line) መብት እንዳላቸው መገንዘብ፣ ከሌሎች የሚመጣው ጫና እንዴት አስቸጋሪ እንደሚያደርግባቸው መፈተሽ፣ እና በበርካታ በሕይወታቸው አካበቢዎች ዙሪያ፣ የት መስመሩን ማስመር (draw the line) እንዳለባቸው በየግል-ሁኔታቸው ማወቅ።
4. **ትምህርት/Lesson 4፡ መስመሩን የማስመሪያ (Drawing the Line) እርምጃዎች (ክፍል/Part 1) –** መስመሩን የማስመሪያው እርምጃዎችን እና ውጤታማ በሆነ እና ውጤታማ-ባልሆነ ግንኙነቶች መካከል ያለውን ልዩነቶች - ማወቅ እና ማሳየት።
5. **ትምህርት/Lesson 5፡ መስመሩን የማስመሪያ (Drawing the Line) እርምጃዎች (ክፍል/Part 2) –** መስመሩን የማስመር እርምጃዎች ላይ ምልከታ ማድረግ፣ እና መስመሩን የት ማስመር እንዳለባቸው ስለማወቅ ውጤታማ-የሆነ ግንኙነቶችን ማድረጊያ የሆኑት የመጀመሪያ ሁለት እርምጃዎችን ማሳየት።
6. **ትምህርት/Lesson 6፡ የሚና-መጫወት አስቸጋሪና-ፈታኝ ነገር (The Roleplay Challenge) –** የ"changing the subject" እና "walking away" እርምጃዎች-ችሎታዎችን መማር፣ እና እነዚህ እንዴት ጥቅም-ላይ እንደሚውሉ ማሳየት፣ አሳማኝ-የሆነ ድምጽን በመጠቀም እና ጠንካራ በሰውነት-የሚገለጽ ቋንቋ (strong body language)ን መጠቀም፣ ያላችሁን የመቋቋሚያ-መጠን ገድቦ ማሳየት (setting your limit)፣ ርዕሱን መቀየር (changing the subject)፣ እና ዞር-ብሎ መሄድ።
7. **ትምህርት/Lesson 7፡ የጓደኞች የአክብሮት መስመር/ገደብ (Friends Respect the Line) -** ግፊት-የሚያደርጉ ባህሪይዎች ለጓደኝነት አደገኛ እንደሆኑ መማር፣ ሌሎች መስመር-አስምረው ገደብ የሰጡትን ነገሮች በማክበር፣ የማህበራዊ ባህሪዎችን ማሳየት።

***መደበኛ-ደረጃ ያለው መማር* (Standards of Learning):**
6.10, 6.11, 6.12